# ክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴር የምነግርዎ አለኝ!

አቤ ቶኪቻው
abeto2007@yahoo.com

ወዳጄ እንዴት ሰነበቱልኝ!? ጤና እንዴት ነው? በርታ በርታ እያሉ ነው? ጎሽ! እንዲህ ነው እንጂ! ድሮም እኮ እርስዎ የበረቱ ኖት! አሁን በቅርቡ አደይ መቀሌ ላይ የብሔር ብሔረሰቦች ቀን ተከብሯል። ያው እንደሚታወቀው ኢትዮጵያችን ላይ ላለፉት ረዥም አመታት ሰው ሳይሆን ቀን ነው የሚከበረው። የሴቶች ቀን፣ የህፃናቶች ቀን፣ የአረጋውያን ቀን፣ የባንዲራ ቀን፣ የኤድስ ቀን፣ የመዳን ቀን፣ የብሄር ብሄረሰቦች ቀን… ሁሉም ቀን ይከበራል። ችግሩ ሰው ላይ ነው። ከዚህ ተነስተው ነው እንግዲህ አንዳንድ ግለሰቦች "ሀገሪቷ ቀን የሚከበርባት ሰው የሚቀበርባት" ሆናለች እያሉ የሚያሽሙሩት።

መቀሌን ግን ምነው እንዲህ እዳ አበዙባት? "የከተሞች ቀን" የተባለውን ክብረ በዓል አክብራ በቅጡ ሳትጨርስ ሌላ ክብረ በዓል ደግሞ ገጠማት። "እንዳለሽ ፍርፉሪ ደግመሽ ዳሪ" የተባለች እናት መሰለችኝኮ! ለማንኛውም ጨዋታችን ከመጀመሩ በፊት እንኳን ለብሔር ብሄረሰቦች ቀን በሰላም አደረስዎ! አይዝዎ ወዳጄ ርስዎም የሚከበሩብ አንድ ቀን ይመጣል!

ዛሬ እንኳ እንደው እርስዎም እንዲያውቁት ብዬ እንጂ ወጌ እንኳ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር ነው። ከየትኛው ጠቅላይ ሚኒስትር? አሉኝንዴ? ይቺ ይቺ ነገር ፍለጋ ናት እንጂ ሳይገባዎ ቀርቶ አይደለም። እኮ… ! ታድያ እንደዚህ አይሉኝም ቀጥያለሁ፡ ቆይማ ለመንደርደር እንዲመቸኝ ርዕሴን ደግሜ ልበለው! "ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር የምነግርዎት አለኝ!"
ምን መሰልዎ…

እንግዲህ አሁን ጎረምሳ አይደሉም። ትልቅ ሰው ሆነዋል። ምራቅዎንም ዋጥ አድርገዋል። ምን ምራቅዎን ብቻ ብዙ ነገር ዋጥ አድርገዋል እንጂ… አይደለም እንዴ? የተለያዩ ሚዲያዎች እንደሚዘግቡት ከሆነ በአውሮጳ ባንኮች የካበተ ገንዘብ አልዎት አሉ! (በርግጥ አሉ ነው። እኔ ያለኝ መረጃ ጥቂት መፅሐፍትና ጥቂት ሱፍ ልብሶች ብቻ እንዳልዎት ነው።) ነገር ግን አሉም ቢሆን፤ መረጃ መረጃ ነውና በአውሮጳ ያልዎት ገንዘብ፣ በባለቤትዎ ስም ያለው ንግድ ድርጅቶች በእናት ድርጅትዎ ስር ያሉ አትራፊ እና መጋቢ ድርጅቶች እና ሌሎችንም ስናይ እንደዋዛ "ምራቃቸውን ዋጥ ያደረጉ ትልቅ ሰው ናቸው" ብቻ ለማለት አንደፍርም ይልቅስ "ብዙ ነገር ዋጥ ስልቅጥ ያደረጉ ናቸው" እንልዎታለን። ጎሽ… ታድያ እንደርሱ ከሆነ ሰው የሚልዎትን መስማት አለብዎ ማለት ነው!

ይህውልዎ አቶ መለስ በቅርቡ አንድ ወዳጄን በስልክ አግኝቼው ነበር። ይህ ወዳጄ ርስዎን እና የርስዎን መንግስት ሽሽት ከሀገር ከተሰደዱት መካከል ነው። ይህ ሰው ከሀገር ባይሰደድ ኖሮ እንዴት ሀገሪቷን ሊጠቅም እንደሚችል ሳስበው በእውነቱ እወቅሰታለሁ። በርግጥ አልረገምምም። ምክንያቱም ርግማን የበዛ እንደሆን ምርቃት ይሆናል የሚል ነገር ሰምቻለሁ። አረ ሳልነግርዎ፤ የአዲሳባ እናቶች ምን እንደሚሉዎት ነገሬዎት አላውቅምና… "ይሄ ሰውዬ እድሜውን ያረዘመው የእኛ እርግማን ሳይሆን አይቀርም…" ይሉዎታል። በነገራችን ላይ በርካታ የአገሬ ሰው "ይሄ ሰውዬ" እያለ እንደሚጠራዎ ያውቃሉ…? የለም አይመስለኝም። እኛ ካልነገርንዎ እርስዎ የት ብለው ያውቁታል? ሌላ በነገራችን ላይ እናቶቹ አሁን እርስዎ በሚጠሩት ሰልፍ ሁላ "ሆ!" ብለው የሚወጡልዎ ንግግር ባደረጉ ቁጥር "እልል" የሚሉልዎ ርግማኑ ስላላወረዳቸው እስቲ ደግሞ እንመርቃቸው ብለው ነው! (በርግጥ ይቺ የኔ ጥርጣሬ ናት) አሁንም በርግጥ የፍቅር እንዳልሆነ ግን እርስዎም ያውቁታል። የፍቅር ነው ከተባለ እንኳ የአበሏ ፍቅር እንጂ የርስዎ ፍቅር አይደለም። ደሞ እንዲህም ስልዎ የእኛ ሰው ለገንዘብ የሚገዛ ነው ለማለት አይምሰልዎ… ይተዉ እንጂ ነገር አያጣሙብኝ… (በቅንፍም የስንቱን ህይወት ያጣመሙት ይበቃዎታል እልዎተለሁ! ቅንፍ ለዘላለም ትኑር!)
እውነቴን እኮ ነው የምልዎ የኢትዮጵያ እናቶች እንዴት ከእርስዎ ፍቅር ሊወድቁ ይችላሉ? እንዴ… "ከማይረባ ሽሮ ይሻላል ሽራሮ" ብሎ የዘመተ ልጃቸውን ካስፈጁ በዋላ እኮ ነው ጦርነቱ ራሱ የማይረባ መሆኑን የአራዳ እናቶች ያወቁት! በዘጠና ሰባትስ ቢሆን በአልሞ ተኳሽ ያስገደሏቸው ወጣቶች እናት የሌላቸው መሰልዎ…? ሶማሊያ ላይም ቢሆንኮ የስንቱን እናት ልጅ ካስጨረሱ በዋላ ነው በፓርላማው "ምን አተረፍን?" ቢባሉ "ይህንን ለዚህ ፓርላማ ማሳወቅ ያለብኝ አይመስለኝም!" ብለው ቃል በቃል የተናገሩት። ይንኑም ሲናገሩ እናቶቹ ሰምተው "አይዬ… ቅዱስ ገብርኤል ይሄንን ሰውዬ አልነቅል አልከኝ!" ብለው አኮ አማረዋል። እረ ሌላም ብዙ ብዙ የሚያማርር ነገር አልዎት! እቆጥብኩ ብነግርዎ ይሻላል…

ለማንኛውም አሁን ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር የምነግርዎ ነገር አለኝ…

እናልዎ በቅርቡ ስልክ የደወለልኝ ስደተኛ ወዳጄ እርስዎ በሚያስተዳድሯዋት ሀገር ላይ ትንሽ ቀናት ቢቆይ ኖሮ ማንቁርቱን ተይዞ እስር ቤት ሊወረወር ነበር። ልብ ያድርጉ… እንደ አቶ ያረጋል አይሸሹም ሙስና ውስጥ አልተዘፈቀም። እንደ አቶ ታምራትም ስኳር አላሰም። ግን እስር ቤት ሊገባ ጥቂት ሲቀረው "እኛም ነቅተናል ጉድጓድ ምሰናል!" ብሎ እብስ አለልዎ… ታድያልዎ እኔም አቻ አገኘሁ ብዬ ገና

እንደደወለልኝ ወደሀገራችን መቼ ነው የምንመለሰው? ብዬ ብለው… “እንጃ!” አለኝ። “እንጃ” ሲል አንድ ቃል ትመስላለች፤ “እንጃ ስትል ምን ማለትህ ነው?” ብለን እንተንትናት… እንጃ ሲል ምን ማለቱ መሰልዎ፤ “የአፍሪካ መሪዎች ስልጣን ላይ ሲወጡ ዕድሚያቸው መቋጫ የለውም። ከጥይትም ከእግዜሩም ሞት የሚጠብቃቸው አንዳች “አርዝም አደንድን!” ሳይወስዱ አይቀሩም እናም እርሳቸው እያሉ መመለሻዬን እንጃ” ማለቱ ነው። ልብ አሉልኝ እርስዎ በህይወት እያሉ መመለስን ይህ ወዳጄ በፍፁም አያስበውም ማለት ነው። እንዲህ አይነት ስንትና ስንት ሰዎች በስደት ላይ አሉ መሰልዎ… ውይ የኔ ነገር ይቅርታ… ውጪ በወጡ በገቡ ቁጥር በተቃውሞ ሰልፍ የሚቀበሉዎት ኢትዮጵያውያንን ብዛት እርስዎ መቼ አጡትና ነው ላስረዳዎ የምሞክረው? ደሞኮ እርስዎ ጉዞ በሚያደርጉ ጊዜ ወይ ስራ በዝቶበት ወይ ደግሞ ደክሞት የሚቀረው ሳይቆጠር ነው። ታድያ ይሄ ሁሉ ኢትዮጵያዊ እርስዎ በህይወት እያሉ ወደ ሀገር ቤት የመመለስ ተስፋ የለውም…! ለምን መሰልዎ፤ መቼም እርስዎ በህይወት እያሉ አይኖ እያየ ስልጣን የሚለቁ አይነት አይደሉም። እርስዎ ስልጣን ካለቀቁ ደግሞ እርስዎን የሚጠየፉ በሙላ በሀገር መኖር አይችሉም። እንኳንስ ለጠላዎትና ለእኛ ለወዳጅዎም አልሆኑም…(አልን እኔ እና ታምራት ላይኔ (አንዳንዴም ፈገግ እያሉ ያንቡብን እስቲ እስከመቼ ኮስተር ብለው!))

እና በውጪ ሀገር ያለው ኢትዮጵያዊ በይፋ እንዲሁም በሀገር ውስጥ የሚኖረው ደግሞ በሆዱ የእርስዎን ህይወት መቋጫ እየለመነ ይገኛል። እኔ ግን እውነቱን ለመናገር ቀልቦን እንዲመልስልዎ እንጂ ከዛ በዘለለ ክፉ አልመኝልዎትም። የምፈራው ግን በኔ ፀሎት ብዛት ቀልብዎ ተመልስልዎ፤ ቀለብ ያሳጡትን ህዝብዎን ሲያስተውሉ በስራዎ ተፀፅተው እንደ ከሀዲው ይሁዳ ራስዎን እንዳያጠፉ እፈራልዎታለሁ። (ውይ የኔ ነገር እረ የሰይጣን ጆሮ አይስማ…! ከስልጣንዎ ወርደው፣ ይቺ ወንበር ሌላ ሰው ተቀምጦባት፣ በሰላም መልቀቅ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ሳያሳይዎማ፤ ክፉ አያምጣብዎ።)

እናልዎ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር የምነግርዎ አለኝ… ብዬዎም አይደል ጨዋታዬን የጀመርኩት። አዎ እውነቴን ነው የምነግርዎት አለኝ። እኔ መቼም ምን ያህል አሳቢዎ እንደሆንኩ ከእርስዎ የተሰወረ ይሆናል ብዬ አልጠረጥርም። እናም የምመክርዎ የምሬን ነው። ብዙ ሰው ቂም ይዞብዎታል። “ባገኛቸው አለቃቸውም” እያለ የሚዝትብዎ በርካታ ነው። እና አንድ ዘዴ ታየኝ በርግጥ ይህንን ዘዴ ከአሁን በፊትም ተመክረውት ይሆናል። እኔ ግን ቤተሰብ ነኝና፣ እኔ ግን አሳቢዎ ነኝና፣ እኔ ግን አድናቂዎ ነኝና፣ የእኔን ምክር ሊሰሙ ይችላሉ ብዬ እገምታለሁ። እናልዎ ሰዉ ሁሉ “እንደወገብ ቅማል” ጥምድ አድርጎ ይዞዎ “ባገኛቸው አለቃቸውም” እያልዎ ነው። ይህው መቼ ዕለትም በታላቁ ሩጫ ላይ “ሳንፈልጋቸው ሃያ አመታቸው” እያለ ሲዘፍን የነበረው ህዝብ ገሚሱ ከመንግስት በጀት ቲሸርት የተዛለት ሁላ ነው። ይሄ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለራስዎ ልተውሎት ስንቱን ነግሬዎ እችለዋለሁ?

እና ምን መሰልዎ የምነግርዎ… ብዙ ሰው ጠምዶታል። እሺ ይሁንልዎ “አምስት ሚሊዮን አባል” ይወድዎታል። ቀሬው ሰባ አምስት ሚሊዮን ህዝብ እና ከሀገር የወጣው የአገርዎ ሰው ደግሞ በጥቅሉ ማለት በሚያስደፍር ሁኔታ፤ ፖለቲካ የሚችለው እየተነተነ ፖለቲካ የማይችለው ደግሞ ቢያንስ ቢያንስ የጠጉርዎን ነገር እያነሳ የማያብጠለጥልዎ የለም። እውነቴን ነው የምልዎ…! ሰዉ ጥምድ አድርጎታል። እንኳን ሌላው ቀርቶ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን፣ በአዲስ ዘመን በሬድዮ ፋና፣ በዋልታ በወዘተ. የሚገኙ ልማታዊ ጋዜጠኞችዎ ራሳቸው እንጀራ ሆኖባቸው እንጂ ስራቸውም ሆነ አስተዳደሩ እንዴት ድብር እንዳላቸው አይጠይቁኝ። ነጋ ጠባ ግምገማ፣ ነጋ ጠባ ሂስ መዋጥ፣ ነጋ ጠባ መዋጮ፣ ነጋ ጠባ ውሸት፣ ነጋ ጠባ ፕሮፓጋንዳ… አንድ ቀን ምርር ያላቸው እለት እዛው ስቱዲዮ ውስጥ ሆነው “የዘመናት ብሶት የወለደው ጋዜጠኛ ለሰፊው ህዝብ ጥቅም ስቱዲዮውን ተቆጧጥሮታል!” ብለው እንዳያውጁ ሁላ እፈራልዎታለሁ።

ከዚህ በፊት በተለያዩ ፅሁፎቼ ለመጠቆም እንደሞከርኩት “ልማታዊ ጋዜጠኞቹ” አንዳንዴ በሚያስታውቅ መልኩ አንዳንዴ በማያስታውቅ መልኩ ሽሙጣዊ ዘገባ እያቀረቡ ነው። እንደ ምሳሌ አንድ ጊዜ በራዲዮ ፋና የሰማሁትን ዘገባ ልንገርዎ… ወቅቱ እነ እስክንድር ነጋ እና አንዷለም አራጌ የታሰሩበት ወቅት ነበር። ታድያልዎ ጋዜጠኛው ዜናውን ምን ብሎ አነበበው መሰልዎ “አቶ አንዷለም አራጌ እና እስክንድር ነጋ ግንቦት ሃያ ከተባለው አሸባሪ ድርጅት ጋር ተባብረው ሲሰሩ ነበር…” አለልዎ… ልብ ብለዋል “ግንቦት ሃያ ከተባለ አሸባሪ ድርጅት ጋር…!” እና ታድያ ይሄ ምን ያመለክትዎታል…? እንዴ ሽሙጥማ ይግባዎ እንጂ!

አዲሳባም እያለሁ ከአሁን አሁን እነግርዎታለሁ ስል ሌሎች ጉዳዮች ይዘውኝ ነው ያልነገርኩዎ… እንጂ ሰው ጠልቶታል። ፎቶግራፍዎ በየቦታው ተሰቅሎ ሲያዩት የፍቅር አይምሰልዎ። የኮነሬል መንግስቱን ፎቶግራፎች ያስታውሱ።

የየሰዉን “ፌስ ቡክ” ቢያገላብጡ… እንዴት እንዴት መቀለጃ እንደሆኑ አይጠይቁኝ። በመዲናዎ ውስጥ ያሉ የህዝብ እና የካፍቴሪያ መፀዳጃ ቤቶችን ለአፍታ ቢመለከቱዋቸው እውነተኛውን የህዝቦን ስሜት ይረዳሉ። እና ምን ይሻላል? ብለው የጠዩቁኝ እንደሆነ እውነትም ብልህ መሪ ኖት ማለት ነው። ምን ይሻላል መሰለዎ…!?

ግዴየልዎትም ይሄ ህዝብ አንድ ቀን እጅግ በጣም፤ ከእጅግ በጣምም በላይ ተማሮ በደህናው ግዜ ታትሞ የተባዛ ፎቶግራፎትን እያነደደ “በቃዎ” ብሎ ከመቆጣቱ በፊት “መለስ ለፍርድ ይቅረቡ!” የሚል መፈክር ከመሰማቱ በፊት እራስዎ፤ በራስዎ ተነሳሽነት በቃኝ! ይበሉና ታሪክ ይስሩ። ይመኑኝ ይህንን ነገር ዛሬ ነገ ሳይሉ የተገበሩት እንደሆነ በሀበሻ ልብ ውስጥ መልካም የተባለውን ቦታ ያገኛሉ።

ይህንን ምክር ብዙዎች መከረዎት ይሆናል። እኔም ደግሜ እመክርዎታለሁ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴር እባክዎ ይብቃዎ…

እውነቴን ነው የምልዎ የእኔ ምክር ለእርስዎ ከማሰብ የመነጨ ነው። ይመኑኝ… የጤናዎ ነገር እጅግም እንደሆነ እየተነገረ ባለበት በዚህ ወቅት፣ ሰዉ “ጤና አጥተው ጤና ነሱን” እያለ በብዛት በሚያማርርበት በዚህ ወቅት፣ “ሳያስፎግሩ” በሰላም ሹልክ ማለት ማንም “የአራዳ ልጅ” የሚያደርገው፤ “የገባው ሰው” ስራ ነው። “ጀዝባ ላለመባል ብዬ ሲጃራ ማጤስ ጀመርኩ” እንዳሉን ሁሉ አሁንም የምልዎን ካላደረጉ ከተመሳሳይ ስም ማምለጥዎን እጠራጠራለሁ። እና የተከበሩ ሆይ እባክዎን ይብቃዎ… እናም ሀገሪቷ “ባገኘው አለቀውም” ከመባባል ትንፃ! አይዝዎ አይፍሩ የሆነ ቀን ጠዋት ሲነሱ ይህንን ይወስኑ!

“በቃኝ!” ይበሉ

በመጨረሻም
ወዳጄ አሁን መሰነባበቻችን መስመር ላይ ደርሰናል። እስቲ ቸር ያሰማን!

አማን ያሰንብተን!

December 10, 2011